# ምድብ አምስት (ከ10ኛ — 12ኛ) ክፍል
## 35 ኛ ሳምንት
## *መንፈስ ቅዱስ - የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች*

**የትምህርቱ ዓላማ**

- ስለመንፈስ ቅዱስ መማር የጀመርነው የመጨረሻ ክፍል የዛሬው ትምህርት ነው፡፡
- በዚህ ትምህርታችንም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ምን እንደሆነና መንፈስ ቅዱስ በአማንያን ሕይወት ያለውን በጎ ተጽእኖ እንማራለን፡፡

**የሚጠኑ ጥቅስ**

- ***" የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ደስታ፣ሰላም ትዕግስት፣ቸርነት፣በጎነት፣እምነት፣የውሃት፣ራስን መግዛት ነው፡፡"*** ገላ 5÷22-23

**የትምህርቱ ትኩረት**

- ትክክለኛ ክርስቲያንን ስታስተውሉ ክርስቲያን ካልሆነና በስም ብቻ ክርስቲያን ከሆነ ሰው በአስተሳሰቡ፣በጠባዩና በአኗኗሩ ከፍተኛ ልዩነት ያለው ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡
- እነዚህ ልዩነቶች ናቸው እውነተኛ ክርስቲኖች የሚታዩ ሌሎች የሌሎቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የሚባሉት፡፡
- አሁን የምንነጋገርባቸው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች፡-

  (ሀ) በገላትያ የተጠቀሱ
- "***የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ደስታ፣ሰላም ትዕግስት፣ቸርነት፣በጎነት፣እምነት፣የውሃት፣ራስን መግዛት ነው፡፡*** ገላ 5÷22-3

  (ለ) በኤፌሶን የተገለጠው "      " ኤፌ 1÷17-18 (ካለፈው ሳምንት copy paste) ናቸው፡፡

(ሀ) **<u>*በገላትያ መልእክት ምዕ 5÷22-23 የተገለጡት ፍሬዎች*</u>** እነኚህ በኔና በእናንተ ውስጥ ያሉ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ናቸው፡፡ ይሄም አስተሳሰባችንን፣ ፍላጎቶቻችንን፣ ጠባያችንና ኑሮአችንን የሚዳስስ ነው፡፡ እነዚህ ፍሬዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

<u>ፍቅር</u> ፍቅር የጽድቅ ሁሉ መሠረት *ነው፡፡ **"ፍቅር ይታገሣል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፣ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ በደልን አይቆጥርም ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም ሁሉን ይታገሣል፣ ሁሉን ያምናል፣ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፣ በሁሉ ይጸናል፡፡*** 1ኛ ቆሮ 13÷4-8

<u>ደስታ</u> የክርስትና ዋና ግብ የሰው ልጅ ደስታ ነው፡፡ ወንጌል ማለትም "የምስራች" — "የደስታ ዜና" ማለት ነው፡፡

- ***"በጌታ ደስ ይበላችሁ፡፡"*** ፊልጰ. 4÷4

<u>ሰላም</u> ከደስታ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ***"የእግዚአብሔር መንግስት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት"*** ሮሜ 14÷17
ፍቅርና ደስታ በአማንያን ልቦና ሰላምን ይሠጣሉ፡፡
<u>ትዕግስት</u> በንዴት ምክንያቶች ባለመቆጣት መረጋጋትና የሌሎችን ክፉ ድርጊት መቻልና ማለፍ ናቸው፡፡ ጌታችን ትዕግስትን በትክክል ያሳየን ምሳሌያችንም ነው፡፡

<u>ቸርነት</u> የቁጣ ተቃራኒ ነው፡፡ "እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት፤ ጭከናው በወደቁት ላይ ነው፣በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፤ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ" ሮሜ 11÷22 ***"እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፣ ምሕረትን፣ ርህራሄን፣ ቸርነትን፣ ትሕትናን፣ የዋህነትን፣ ትዕግስትን ልበሱ፡፡*** ቆላ 3÷12

<u>በጎነት</u> ቸርነት ለበጎነት ያዘጋጀናል ***"... ወንድሞቼ ሆይ፣ በበጎነት ራሳችሁ እንደተሞላችሁ እውቀትም ሁሉ እንደሞላባችሁ፣ እርስ በርሳችሁም ደግሞ ልትገሠጹ እንዲቻላችሁ ስለ እናንተ ተረድቼአለሁ፡፡"*** ሮሜ 15÷14

<u>እምነት</u> ትክክለኛ እምነት የበጎ ሕይወት መሠረት ነው፡፡***"ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና፡፡"*** ዕብ.11÷6

**<u>*የውሃት*</u>** የውሃት አንድ ሰው ጥፋተኛ መሆኑንም እወቅን አለመፍረድ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዋህ እንድንሆን ሲያስተምረን፡፡ ***"ከእኔ ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና፡፡"*** ብሎዋል፡፡

**<u>*ራስን መግዛት*</u>** ኃጢአት ከመስራት ራስን መግዛት ነው፡፡ ***"ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፣ በበጎነትም እውቀትን፣ በእውቀትም ራስን መግዛትን፣ ራስንም በመግዛት መጽናትን፣ በመጽናትም እግዚአብሔርን መምሰል፣ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፣ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ፡፡"*** 2ኛ ጴጥ 1÷5

(ለ) **<u>በኤፌሶን 1÷17-18 የተገለጠው ፍሬ</u>** በእውነተኛው ክርስቲያናዊ ስብዕና ጥበብና መገለጥ አሉ፡፡ እነዚህም ስለእግዚአብሔር እንዲመሰክርና በእግዚአብሔር ክብርና ጸጋ እንዲኖር ያስችሉታል፡፡ይህም በምድር ሰማያዊ ሕይወትን እንዲያጣጥም ያደርጉታል ማለት ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጠውም "…. **<u>የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ</u>** …" (ኤፌ 1÷17-18 ኮፒ ፔስት)

**<u>*ምን ተማርን*</u>**

(1) ስንጠመቅ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል ከታዘዝንና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የቀና ሕይወትና ሕብረት ካለን ከላይ የተገለጡት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የእኛ ይሆናሉ፡፡

(2)በቤተክርስቲያን ያለፋትን ቅዱሳን ስንመለከት ታላቅ በረከቶችን ሲቀበሉና የመንፈስ ቅዱስን ፍሬዎች በሕይወታቸው ሲያፈሩ እናስተውላለን፡፡ ለዚህም ነው ሻማ ከስዕሎቻቸው ስር የምናበራው፡፡ ሻማና ጧፍ ከተጋገረ ቅባት ይዘጋጃሉ፡፡ ቅባቱ (ዘይቱ) የመንፈስ ቀዱስ ምሳሌ ነው፡፡ እሳቱ ሲቃጠል፣ ቅባቱ ይቀልጣል፡፡ ብርሃንም ይገኛል፡፡ (ማለትም ከመልካም ሕይወት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ይገኛል፡፡)

## ***ይቆየን፡፡***